# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ይሁንታ መድረክ – ዩናይትድ ኪንግደም

## *Ethiopian National Consensus Forum - UK*

*Tel: 0044 (0) 207 589 7212 Ext.(230)*
*Mobile: 07939 956086*

*Email: encfuk@yahoo.co.uk*
*17 Prince's Gate , London ,SW7 1PZ*

ቀን፣ ሐምሌ 16 ቀን 1999 ዓ.ም.

ቁጥር፣ የብይመ 010/11/99

## በእስር ላይ ለነበሩ የቅንጅት አመራሮች የተደረገውን ይቅርታ በተመለከተ ከብሔራዊ ይሁንታ መድረክ የተሰጠ መግለጫ

ሰሞኑን መንግስት እስር ላይ የነበሩ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ርቲ መሪዎችና ጋዜጠኞች ጥፋተኝነታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲደረግላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በአንክሮ ተመልክቶ ከሕግ ጋር በማይጣረስ መልኩ ይቅርታ ማድረጉ እጅግ ደስ ያሰኘን መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

የብሔራዊ ይሁንታ መድረክ በ1997 ዓ.ም. ከተካሄደው ምርጫ ማግስት ጀምሮ የነበረውን አደገኛ አዝማሚያ በመገንዘብ የምርጫው ተፎካካሪዎች ችግሩን በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ለሁሉም አካላት ጥሪ ማቅረቡ የሚታወስ ነው። ያለመታደል ሆኖ ነገሮች ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ሂደው አገራችንና ሕዝባችን አሳዛኝና አላስፈላጊ ወደሆነ ትርምስና ምስቅልቅል ውስጥ ለመግባት ተገደው ነበር።

ሆኖም ግን መንግስት ችግሩ ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ ሕገ-መንግስቱን በማስከበርና ጥፋተኞችን ሕግ ፊት በማቅረብ ተገቢውን የፍርድ ውሳኔ እንዲያገኙ ካደረገ በኋላ የአበውን ዕውቀትና ተሞክሮ ተጠቅሞ ለእስረኞች ይቅርታ ማድረጉ አስተዋይ አዕምሮና ልቡና ላለው ሁሉ ለአገራችን የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ መሆኑ የማይሳት ሀቅ ነው።

የአገር ሽማግሌዎችም ይህንን ሁኔታ ተገንዝበው ከተሳሪዎቹም ከመንግስት ጋር ያለመታከት ባደረጉት ሽምግልና ጥንታዊና ነባር የችግር አፈታት ዘይቤ ምንጊዜም ዘመን የማይሽረው የአገር ቅርስ መሆኑን በማስመስከራቸው ሊመሰገኑ ይገባል እንላለን።

መንግስትም ይህንን ችግር ለመፍታት በሕግም ሆነ በሽምግልና ያከናወናቸው ተግባራት ወደፊትም አገራችን ውስጥ በየጊዜው የሚከሰቱ ሌሎች አዳዲስ ችግሮችን ለመፍታት መፍትሔዎች አገር በቀል እንዲሆኑ  የሚያደርግ መሆኑን ስለሚጠቁም መድረካችን በአዎንታዊ መልኩ የሚመለከተው ይሆናል።

ለወደፊቱም መንግስት በሕግና ሥርዓት ላይ የተመሰረተ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ቅድሚያ በመስጠት ለዚህ ሂደት በአጋዥነት ደግሞ የአበውን የሽምግልና እንዲሁም ተዝቆ ከማያልቀው ሌላው የባህል ቅርሳችን በመፈተሽ እንደየአግባብነቱ ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ እንዲጠቀምበት ለመጠቆም እንወዳለን።

ሰሞኑን የታየው አዎንታዊ የፖለቲካ ክስተት የሚጠቁመው ለሀገራችን የዲሞክራቲክ ስርዓት ግንባታ መሠረት የሆነው የሕግ የበላይነት መረጋገጡና በኢትዮጵያችን ለዘመናት ያለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ትልቅ አስተዋጽኦ ሲያደርግ የቆየው የሽማግሌዎችና የአበው ምክክር የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ችግር ለመፍታት ያለው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ጎልቶ መታየቱ ነው። በዚህ ሂደት አሸናፊና ተሸናፊ የሌለበት ሁሉም አሸናፊ የሆነበት አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ ተከፍቷልና በኢትዮጵያ የዲሞክራቲክ ሥርዓት ለመገንባትና ድህነትን ከአገራችን ለማስወገድ የማያቋርጥ ጥረት የምናካሂድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአግባቡ ልንጠቀምበት ይገባል።

በመጨረሻም የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ደጋፊዎችም ሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ለተሳተፉት የሀገር ሽማግሌዎች እንዲሁም ጉዳዩ አሳስቦን ለነበረው ወገኖች ሁሉ እንኳን ደስ ያለን እያልን አዲሱን ሚሊኒየም በደስታ፣ በፍቅርና በመከባበር ለመቀበል እንዘጋጅ እንላለን።

የብሔራዊ ይሁንታ መድረክ
ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
ለንደን